# ሆሣዕና

በርእሱ እንደ ተገለጸው፣ ስምንተኛው እሑድ ሆሣዕና ይባላል። ሆሣዕና ቃሉ እብራይስጥ ሲሆን፣ ትርጉሙ ደግሞ ሁለት ነው:-

፩ኛው መድኃኒት ማለት ሲሆን፣ ፪ኛው ትርጉሙ ደግሞ ምስጋና ማለት ነው። በዚህ ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከደብረ ዘይት ጫፍ ጥቂት ዝቅ ብሎ ከሚገኘው ቤተ ፋጌ ከተባለው ቦታ ጀምሮ፣ ደቀ መዛሙርቱ ባቀረቡለት አህያ ላይ ተቀምጦ፣ ወደ ኢየሩሳሌም ሲጓዝ ጌታችንን ያጀበው ሕዝብና ደቀ መዛሙርቱ በቀኝ በግራ፣ በፊትና በኋላ ሆነው «ሆሣዕና» ብለው እየዘመሩ ስለ ተጓዙ በዚህ ምክንያት ዕለቱ «ሆሣዕና» ይባላል። በዚያ ቀን የሚዘምረውና የሚነበበውም፣ «ሆሣዕና፤ ሆሣዕና» የሚል በመሆኑ ዕለተ እሑዱ ሆሣዕና እየተባለ ይጠራል፤ የምስጋና ቀን ማለት ነው።

የሆሣዕናን ታሪክ እንደሚከተለው እንመልከት:-

የሆሣዕና ታሪክ በአራቱም ወንጌላውያን የተጻፈ ሲሆን፣ እዚህ ላይ ከቅዱስ ማቴዎስ እንጀምራለን፤ «ወደ ኢየሩሳሌም ቀርበው ወደ ደብረ ዘይት፤ ወደ ቤተ ፋጌ ሲደርሱ ያን ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ላከ፣ ‹በፊታችሁ ወዳለች መንደር ሂዱና በዚያም የታሰረች አህያና ውርንጫዋን ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁም አምጡልኝ፤ ማንም አንዳች ቢላችሁ ለጌታ ያስፈልጉታል በሉ› ብሎ አዘዛቸው። ‹እንግዲህ ይህ የሆነው «ለጽዮን ልጅ እነሆ ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ በአህያ ላይና በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ይመጣል በሉአት ተብሎ በነቢይ የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ነው» (ዘካ.፱፥፱)።

ደቀ መዛሙርቱም ሄደው ኢየሱስ እንዳዘዛቸው አደረጉ። አህያይቱንና ውርንጫዋንም አመጡለት፤ ልብሳቸውንም በአህያይቱና በውርንጫላዋ ላይ ጫኑ፤ እሱም ተቀመጠባቸው። ከሕዝቡም እጅግ ብዙዎች ልብሳቸውን በመንገዱ ላይ ያነጥፉ ነበር። ከፊቱም ከኋላውም ያለው ሕዝብ ‹ሆሣዕና! ለዳዊት ልጅ፣ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፤ ሆሣዕና በአርያም› እያሉ ይጮሁ ነበር። ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ መላ ከተማይቱ፣ ‹ይህ ማን ነው?› ብላ ተናወጠች» (ማቴ.፳፩፥፩–፲፩)።

ሕዝቡም፣ ‹ይህ ከገሊላ ናዝሬት የመጣ ነቢዩ ኢየሱስ ነው› አሉ። በዚህ መልክ በማርቆስ፣ በሉቃስና በዮሐንስ ወንጌል በተመሳሳይ ሁኔታ ተመዝግቦአል። ቀደም ብለን እንደ ገለጽነው፣ «ሆሣዕና ለወልደ ዳዊት (የዳዊት ልጅ) ሆሣዕና በአርያም» ማለታቸው ምስጋና ለዳዊት ልጅ፣ ምስጋና በአርያም ማለታቸው እንደ ሆነ ቅዱስ ሉቃስ በጻፈው ወንጌል ተረጋግጦአል።

ቃሉም፤ «ወደ ደብረ ዘይትም ቁልቁለት በደረሱ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሁላቸው ደስ አላቸው። ተአምራትንም ስላዩ በታላቅ ድምፅ እግዚአብሔርን ሊያመሰግኑ ጀመሩ። በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ንጉሥ የተባረከ ነው። በሰማይም ሰላም፤ በአርያምም ምስጋና (ክብር) አሉ» (ሉቃ.፲፱፥፴፰) ይላል።

ስለዚህ በአራቱም ወንጌላውያን፤ «ሆሣዕና! ሆሣዕና!» ተብሎ የተነገረው ምስጋና ወይም ክብር ማለት መሆኑን መገንዘብ ይገባል። ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም በተወለደ ጊዜና ከቤተ ፋጌ ወደ ኢየሩሳሌም በአህያ ተቀምጦ በተጓዘ ጊዜ የተሰማው ምስጋና ተመሳሳይ ነው።

የሰማይ ሠራዊት (መላእክት) ጌታችንን በአካለ ሕፃን በቤተልሔም ዋሻ በበረት ተኝቶ በጨርቅ ተጠቅልሎ ባዩት ጊዜ፤ «ምስጋና ለእግዚአብሔር በአርያም ሰላም ለምድር...» ብለው አመሰገኑ (ሉቃ.፪፥፲፬)።

ከቤተ ፋጌ እስከ ኢየሩሳሌም ባለው መንገድ ደግሞ፤ ጌታችን በፈረስ ወይም በበቅሎ ሳይሆን፤ በተናቀች እንስሳ በአህያ ተቀምጦ ያዩት ደቀ መዛሙርቱና ሕዝቡ ሁሉ ትሕትናውን አይተው በመደሰትና በማድነቅ፤ «ሆሣዕና (ምስጋና) ለዳዊት ልጅ» ብለው አመሰገኑት። ጌታችንም በእናቱ ሐረገ ትውልድ የዳዊት ልጅ ነውና፤ «ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ» ብለው አመሰገኑት።

ጌታችን ወደዚህ ዓለም የመጣው የተዋረዱትን ከፍ ከፍ ለማድረግና ትሕትናን ለማስተማር ነውና በተዋረደች አህያ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ። ነገር ግን የማያልፍ ንጉሥ (ንጉሠ ዘላለም) መሆኑን የተረዱ ደቀ መዛሙርቱና ያጀቡት ሕዝቦች ልብሳቸውን ከጫንቃቸው እየገፈፉ፤ የዛፎችን ቅርንጫፍ፤ ዘንባባውንና የወይራውን ቅጠል እየቈረጡና በየመንገዱ ላይ እያነጠፉ፤ «ሆሣዕና! ሆሣዕና!» እያሉ በመጮኽ አመስግነውታል። ጌታችን መድኃኒትና ሕይወት መሆኑን ስለ ተረዱም የሕይወት ምልክት የሆነውን ለምለሙን የዛፍ ቅርንጫፍ በመንገድ ላይ ጐዘጐዙለት። በነቢዩ ዘካርያስ የተነገረ ትንቢትም ተፈጸመ። ትንቢቱም፤ «አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ፤ እጅግ ደስ ይበልሽ፤ አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ፤ እልል በይ! እነሆ ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው፤ ትሑትም ሆኖ በአህያም በአህያይቱም ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወዳንቺ ይመጣል» ተብሎ ተነግሮ ነበር (ዘካ. ፱፥፱)። በትንቢቱም መሠረት ጌታችን ግማሹን መንገድ በእናቲት አህያዋ፤ ቀሪውን መንገድ ደግሞ በውርንጫዋ ላይ ተቀምጦ፤ ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ እንደ ገባ የመጽሐፍ ቅዱስ መተርጕማን ያስተምራሉ።

ከላይ በተገለጸው መሠረት፤ «ሆሣዕና (ምስጋና ለዳዊት ልጅ) በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው፤ ሆሣዕና በአርያም!» እያሉ መላዋ ኢየሩሳሌምና ሕዝቡ በሙሉ፤ ይህ ማን ነው ብለው በመናገር ተናወጡ። ሕዝቡም ይህ ከናዝሬት የመጣ፤ «ነቢዩ ኢየሱስ ነው» ብለው መለሱ (ማቴ.፳፩፥፱–፲)።

ጌታም ከቤተ መቅደሱ እንደ ደረሰ በመቅደሱ ቅጽር ግቢ ሲሸጡና ሲለውጡ የነበሩትን ሁሉ አስወጣ፤ ለመሸጥ ቀርበው የነበሩትንም እንስሳት ሁሉ ወደ ውጪ አስወጣ፤ ተደርድረውም የነበሩትን የገንዘብ ለዋጮችንም ጠረንጴዛዎች ገለበጠ፤ የገመድም ጅራፍ አበጅቶ ሁሉን እየገረፈ አስወጣ «ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፎአል፤

እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት» አላቸው (ማቴ.፳፩፥፲፪፤ ዮሐ.፪፥፲፫–፲፯)።

እዚያም በመቅደሱ አደባባይ ተቀምጠው የነበሩትን ዕውሮችንና አንካሶችን ፈወሳቸው። የካህናት አለቆችም በዚያን ጊዜ ሕዝቡ በሙሉ ጌታችንን «ሆሣዕና» እያሉ ሲያመሰግኑ ይሰሙ ነበር። ሕፃናትና ልጆችም «ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ (ለኢየሱስ)» እያሉ በመጮኽ ጌታን ሲያመሰግኑ ተቈጡና ለጌታ፡ «እነዚህ የሚሉትን አትሰማምን?» አሉት።

ኢየሱስም፡ «እሰማለሁ፤ ከሕፃናትና ከሚጠቡት አፍ (አንደበት) ለራስህ ምስጋና አዘጋጀህ ተብሎ የተጻፈውን ቃል ከቶ አላነበባችሁምን?» አላቸው (ማቴ.፳፩፥፲፭–፲፯)።

የሊቃነ ካህናቱን ቅንዓት አስመልክቶ በግዕዙ፡ «ወሊቃነ ካህናትሰ ኢሐወዞሙ፤ (ሊቃነ ካህናቱ ግን ደስ አላላቸውም)» ይላል (ማቴ.፳፩፥፲፭)። አዎን፡ ጌታ ሲመሰገን በማየታቸው ቀኑ፤ ደስ አላላቸውም «ለምን ያመሰግኑታል?» ብለው ተቈጡ።

«እነዚህ የሚሉትን አትሰማምን? ለምንድር ነው የሚያመሰግኑ? ገሥጻቸው!» አሉት።

ጌታችንም፡ «እውነት እላችኋለሁ፤ እነዚህ ዝም ቢሉ ድንጋዮች ይጮኻሉ (ይዘምራሉ)» ሲል መለሰላቸው (ሉቃ.፲፱፥፴፯–፵)።

በዚህ ዘመንም ጌታ በመመለኩና በመመስገኑ የማይደሰቱ ወገኖች አሉ። ከሰይጣናት ወገን ብቻ ሳይሆን፡ ለምስጋና ከተፈጠረው ከሰው ወገን እግዚአብሔርን በሚያመሰግኑ ወገኖች ላይ ጣታቸውን የሚቀስሩ፤ ጌታን በሚያመልኩና በሚያመሰግኑ ወገኖች ላይ የሚያፌዙ ሰዎች አሉ። በኮሚኒዝምና በኤቲይዝም ስም የመጡት ወገኖችም እንዲሁ ያደርጉ ነበር። እግዚአብሔርም እንዳይመለክ የሚቃወሙ ወገኖች ራሳቸውን ቀና ቀና አድርገው ነበር። በቤተ ክርስቲያንና በእግዚአብሔር ተከታዮች ስደትና ቅጣት ዐውጀው ነበር። በዚያም ምክንያት ለእሥራት፡ ለግርፋት እንዲያውም ለሰማዕትነት ሞት የተዳረጉ ሰዎች እጅግ ብዙ እንደ ነበሩ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡ በሀገራችን በኢትዮጵያና በሌሎች የኮሚኒስት ሀገሮች ተከስቶ የነበር።

በሆሣዕና ዕለት ኢየሩሳሌም በጌታ መመስገን እጅግ እንደ ደነገጠች ተጽፎአል። ኢየሩሳሌም ጌታን አይታ፡ «ይህ ማነው?» ብላ ከጠየቀች በኋላ፡ እርሱ የሰላም ንጉሥ መሆኑን አምና መቀበል ስለ ተሳናት፡ ጌታ በደብረ ዘይት ተቀምጦ ወደ ከተማዋ እያየ፡ «ብታውቂስ ኑሮ ሰላምሽ ዛሬ ነበር፤ ነገር ግን አላወቅሽም፤ ከዓይንሽም ተሰውሮአል...» ብሎ አለቀሰላት (ሉቃ.፲፱፥፵፩)።

ዛሬም የሰላም ንጉሥ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በማያውቁት ወገኖች ላይ ያዝናል፤ ስላላወቁትና ስላልተከተሉትም ያዝናል። «ብታውቂስ ሰላማችሁ ዛሬ ነበር፤ ብታውቂስ ድኅነታችሁ ዛሬ ነበር፤ ብታውቂስ የሰላሙ ንጉሥ ወደ እናንተ መጥቶላችሁ ነበር፤ ብታውቂስ ኑሮ ወደ እኔ የምትመለሱበት ጊዜ አሁን ነበር» እያለ ስለ እልከኞቹና «አናውቅህም» ስላሉት ሁሉ ጌታ ያዝናል።

እኛ ግን ጌታ፥ «ሰላማችሁ ዛሬ ነው» ብሎ ድምፁን ሲያሰማን ፈጥነን እንሰማዋለን፤ «በጎቼም ድምፄን ያውቃሉና ይከተሉኛል» ሲል እንደ ነገረን ድምፁን ሰምተን እንከተለዋለን (ዮሐ.፲፥፬)። ነፍሱንም ስለ እኛ ስለ በጎቹ ሰጥቶአልና እንከተለዋለን (ዮሐ.፲፥፲፮)፤ የከንፈሮቻችን የዘወትር ፍሬ የሆነውን የምስጋና መሥዋዕትም ዘወትር እናቀርብለታለን (ዕብ.፲፫፥፲፭)፤ እርሱ ጌታችን ሁል ጊዜ ሰላማችን ነውና (ኤፌ.፪፥፲፬)። «ሆሣዕና በአርያም ለንጉሠ ሰላም፤ ሆሣዕና በአርያም ለመድኃኔ ዓለም» እያልን እናመሰግነዋለን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

## ቃለ ምዕዳን

ከአባ ገብርኤል ሊቀ ጳጳስ

ዋሽንግተን ዲሲ – አሜሪካ

የካቲት ፲፱፻፺፮ ዓ.ም